

## 1.2. የወለል ስፋት በሳ.ሜ$^2$ ፣ በሜ$^2$ እና በሄክታር መለካት


1. ከዚህ በታች ለተሰጡት ምስሎች ምድባቸውን በማየት ስፋታቸውን ፈልጉ ፡




የአንድ ምድብ ስፋት 1 ሳ.ሜ$^2$




.............. ሳ.ሜ$^2$



.............. ሳ.ሜ$^2$



.............. ሳ.ሜ$^2$



.............. ሳ.ሜ$^2$

LIVEWORKSHEETS

## የቃላት ጥያቄዎች

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

1. ከሚከተሉት ምድቦች ውስጥ የስፋት መለኪያ ምድብ ያልሆነው የቱ ነው ?

   ሀ) ሜትር ካሬ   ለ) ሚሊ ሊትር ካሬ

   ሐ) ሄክታር   መ) ሳንቲ ሜትር ካሬ

2. የአንድ ካሬ የጎን ርዝመት 6 ሜ ቢሆን ስፋቱ ስንት ይሆናል?

   ሀ) 48   ለ) 36

   ሐ) 24   መ) መልስ የለም

3. የአንድ ሬክታንግላዊ ጠለል ምስል ርዝመቱ 10 ሳ.ሜ እና ወርዱ 8 ሳ.ሜ ቢሆን ስፋቱ ስንት ሳ.ሜ$^2$ ይሆናል ?

   ሀ) 84   ለ) 36

   ሐ) 18   መ) 80

4. የአንድ የካሬ ቅርጽ ያለው ካፍቴሪያ ስፋቱ 36 ሜ$^2$ ቢሆን የጎኑ ርዝመት ስንት ይሆናል ?

   ሀ) 5 ሜ   ለ) 6 ሜ

   ሐ) 9 ሜ   መ) 8 ሜ

5. የአንድ ሬክታንግላዊ ጠለል ምስል ስፋት 45 ሳ.ሜ$^2$ እና ወርዱ 9 ሳ.ሜ ቢሆን ርዝመቱ ስንት ሳንቲ ሜትር ይሆናል ?

   ሀ) 7 ሳ.ሜ   ለ) 8 ሳ.ሜ

   ሐ) 5 ሳ.ሜ   መ) 4 ሳ.ሜ

6. የአንድ ካሬ የጎን ርዝመት ዙሪያ ድምር 24 ሳሜ ቢሆን ስፋቱ ስንት ይሆናል?

   ሀ) 28 ሳ.ሜ$^2$   ለ) 48 ሳ.ሜ$^2$

   ሐ) 32 ሳ.ሜ$^2$   መ) 36 ሳ.ሜ$^2$

7. የአንድ ሬክታንግላዊ ጠለል ምስል ርዝመት 12 ሳ.ሜ ሲሆን ወርዱ ደግሞ ከርዝመቱ በ 5 ሳ.ሜ ያነሰ ቢሆን ስፋቱ ስንት ይሆናል ?

   ሀ) 25 ሳ.ሜ$^2$   ለ) 72 ሳ.ሜ$^2$   ሐ) 45 ሳ.ሜ$^2$   መ) 60 ሳ.ሜ$^2$

LIVEWORKSHEETS

8. የአንድ ሬክታንግል ርዝመት 6 ሳ.ሜ ወርዱ ደግሞ 4 ሳ.ሜ ነው ፡፡ ሌላ ርዝመቱ ከመጀመሪያው ሬክታንግል በ 2 ሳ.ሜ የሚበልጥ ሬክታንግል ስፋቱ ከመጀመሪያው ሬክታንግል ጋር እኩል እንዲሆን ወርዱ ስንት መሆን አለበት ?

ሀ) 3 ሳ.ሜ    ለ) 4 ሳ.ሜ

ሐ) 6    መ) 5

9. ርዝመቱ 24 እና ወርዱ ደግሞ 8 ሳ.ሜ የሆነን ክፍል ርዝመቱ 2 ሳ.ሜ ባለው ስኩዌር ሸክላ ለማንጠፍ ምን ያህል ሸክላዎች ያስፈልጉናል ?

ሀ) 60    ለ) 42

ሐ) 48    መ) 52

10. ወርዱ 6 ሳ.ሜ የሆነ ስኩዌር እና ርዝመቱ 4 ሳ.ሜ የሆነ ሬክታንግል እኩል ስፋት እንዲኖራቸው የሬክታንግሉ ወርድ ስንት መሆን አለበት ?

ሀ) 7 ሳ.ሜ    ለ) 8 ሳ.ሜ


ሐ) 6 ሳ.ሜ    መ) 9 ሳ.ሜ

11. የአንድ ስኩዌር ርዝመት 5 ሳ.ሜ ነው ፡፡ ርዝመቱ እጥፍ ሲሆን የምናገኘው ስፋት መጠን ከመጀመሪያው ስፋት በምን ያህል ይበልጣል ?

ሀ) 60 ሳ.ሜ$^2$    ለ) 75 ሳ.ሜ$^2$

ሐ) 25 ሳ.ሜ$^2$    መ) 35 ሳ.ሜ$^2$

12. በአንድ ርዝመቱ 25 ሜ እና ወርዱ 12 ሜትር በሆነ መሬት ላይ ርዝመቱ 9 ሜትር የሆነ የስኩዌር ቅርጽ ያለው ቤት ተገንብቷል ፡ ፡ ቤቱ ያላረፈበት ክፍት ፎታ ስፋት ምን ያህል ነው ?




ሀ) 300 ሳ.ሜ$^2$    ለ) 250 ሳ.ሜ$^2$

ሐ) 219 ሳ.ሜ$^2$    መ) 225ሳ.ሜ$^2$

LIVEWORKSHEETS

13. ዙሪያው 20 ሜ የሆነ ካሬ ክፍል ስፋቱ ምን ያህል ነው ?

ሀ) 12 ሜ$^2$ ለ) 20 ሜ$^2$

ሐ) 25 ሜ$^2$ መ) 16 ሜ$^2$

14. የአንድ ርዝመቱ 7 ሜትር ወርዱ ደግሞ 4 ሜትር ሬክታንግል ቅርጽ ያለው ጠረጴዛ ዙሪያው ስንት ሜትር ይሆናል ?


ሀ) 25 ሜ ለ) 49 ሜ

ሐ) 28 ሜ መ) 22 ሜ

15. ከታች የተመለከተው ምስል ላይ አንድ ርዝመቱ 9 ሳ.ሜ፣ ወርዱ ደግሞ 6 ሳ.ሜ የሆነ ሬክታንግል እና አራት እኩል ቦታ የተከፋፈለ ርዝመቱ 2 ሳ.ሜ የሆነ ስኩዌር ይታያሉ፡፡ ከምስሉ ላይ በቀይ የተቀለመው ክፍል ስፋት ምን ያህል ነው ?

ሀ) 54 ሳ.ሜ$^2$ ለ) 56 ሳ.ሜ$^2$

ሐ) 53 ሳ.ሜ$^2$ መ) 50 ሳ.ሜ$^2$




LIVEWORKSHEETS